# የተፈረካከሰ ርዕዮተ ዓለም እሥረኛው መድረክ በመፍረስ ዋዜማ ላይ

**ዮናስ** 05/09/13

በምርጫ 2002 ዋዜማ ላይ እንደ ፖለቲካ ፖርቲ በጠራ ፖሊሲና ፕሮግራም ሳይሆን በጠላቴ ጠላት አይነት በአንድ አዳር ለመወዳጀት የቻሉት የመድረኩ አባል ፖርቲዎች አመራር አካላት ፍላጎት ስልጣን ነበርና መድረኩ በምርጫ 2002 ሲሸነፍ ለመንገራገጭ ጊዜ አልወሰደባቸውም፡፡

የመድረኩ ጠንሳሽና ዋነኛ ክንፍ ነው የተባለው የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፖርቲ አመራሮች መድረኩ የፀረ ዲሞክራሲያውያን ስብስብ ነው በሚሉና አይደለም በሚሉ አስተሳሰቦች ታምሶ ገሚሱ “በመርህ ይከበር” ተቃውሞ በመገንጠል ሰማያዊ ፖርቲን ሲያቋቁም ይህንኑ የመርህን ይከበር አባላት ሲገፋ የነበረው ወገን ደግሞ የፖርቲውን ስልጣን ተቆናጦ ከመድረክ ጋር ቀጠለ፡፡

ከመድረኩ ጋር በተቀላቀለው የመርህ ይከበር የአንድነት ቡድን አባላት ውስጥም ቢሆን በወቅቱ በተለይ በፌዴራሊዝምና በመሬት ጉዳይ ላይ ጥርት ያለ አቋምና ፕሮግራም እንደሚያስፈልግ እና በተጨባጭ ግን ጉዳዮቹ ከስልጣን በኋላ ለሕዝብ ውሳኔ ይቀርባሉ በሚል የከሰረ አካሄድ ተድበስብሰው ማለፋቸው ተገቢ እንዳልነበረና የትም ሊያደርስ እንደማይችል ለመሞገት ቢሞክሩም በይድረስ ይድረስ መድረኩን ያቋቋሙት የነጠላ ፖርቲዎቹ ባለቤቶች የመድረኩ አመራር በመሆናቸው ከአንድነቱ አካላት የተነሱ ጥያቄዎችን የኢህአዴግ ተለጣፊ አስተያየትና ፖለቲካ ያልገባቸው ግለሰቦች ጭፍን አስተያየት በማለት ዘለውታል፡፡

ከዚያም ነገሩ እንደ ነገር ምርጫም አልነበረምና የሚያነሱበት ጊዜ ጠፍቶ እዛው በውስጣቸው ሲብላላና ሲንከባለል ቆይቶ ከአራት ዓመት በኋላ የአዲስ አበባና የአካባቢ ምርጫ ሲደርስ በለመዱት የምርጫ ዋዜማ ግርግር መሰረት መድረኩን ወደግንባር አሸጋግረናል ሲሉ ከማኒፌስቶ ጋር ብቅ አሉ፡፡

አሁንም በተመሳሳይ መድረኩ እንደመድረክ ባሳለፈው አራት ዓመታት ውስጥ የሰራው አንዳች ነገር እንዳልነበረና ወደግንባርነት ሊያሸጋግረው የሚያስችል ምንም አይነት ፖለቲካዊ ምክንያት እንደሌለ ማስረጃ በማጣቀስ የመድረኩን ወደግንባር ተሸጋግሬያለሁ መግለጫ ፌዝ ነው ያሉት የፖለቲካ ተመራማሪዎች ማኒፌስቶውን በተመለከተም ምንም አዲስ ነገር እንደሌለውና ይልቁንም ገሚሱ ከ97ቱ ቅንጅት ከፊሉ ደግሞ ከዚህም ከዚያም በተቀዱ ፖለቲካዊ ፍልስፍናዎች የተሞላ መሆኑ የመድረኩን መሪዎች ማንነት የሚያረጋግጥ ነው ሲሉ ተችተዋል፡፡ እንደተባለውም አልቀረ

የመድረኩን አካሄድና አመሰራረት ሲተቹና ትክክል እንዳልሆነ ሲያመለክቱ የነበሩ ግለሰቦች “ብለን ነበር” ለማለት የሚያስችላቸው አጋጣሚ አሁን በመድረኩ ላይ የተፈጠረ ሲሆን ይኸውም መድረኩ በመፍረስ አደጋ ላይ የመገኘቱ ተጨባጭ ሁነቶች መታየት መጀመራቸው ነው፡፡

መድረኩ ያጋጠመው የመፍረስ አደጋ መንስኤ የመድረኩ የተፈረካከሰ የርዕዮተ አለም ስብስብና እስረኛ መሆን ነው የሚለው የዚህ መጣጥፍ ፀሐፊ እምነት ነው፡፡ ስለሆነም በመድረኩ ፈጣሪነት ግንባር ቀደም ተዋናይ የነበረውና የመድረኩ አባል ፖርቲ በመሆንና ባለመሆን አባላቱ ውዝግብ ውስጥ ገብተውበት የነበረው አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ የአንድነት ጠንሳሽ የነበሩትን እና የመድረኩ አባል መሆን የለብንም ያሉትን የመርህ ይከበር አባላት የኢህአዴግ ተለጣፊና ፀረ ዴሞክራሲያዊ ቡድን በማለት ካባረረ በኋላ ዛሬ ደግሞ እራሱ አንድነት ራሱን እንደቻለ አንድ ፖርቲ የመድረኩ አባል መሆን አለበት ወይስ የለበትም? በሚል ለወራት የተጠና ነው ከተባለው የጥናት ውጤት ጋር በማያያዝ ሃሳቤን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

መድረኩ በተመሰረተበት ወቅት ብዙ ልዩነት ስላለን የመድረኩ አባል መሆን አንችልም ያሉ አባላትንና አመራሮችን ፀረ ዲሞክራሲያዊ ናችሁ በማለት አባሮአቸው የነበሩትና አሁን አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ አመራሮች ተመልሰው የመድረኩ አባል መሆን ይገባናል ወይስ ሌላ አማራጭ አለን? በማለት አንድ ኮሚቴ ያዋቅራሉ። ይህ ኮሚቴ መድረኩ በተመሰረተበት ወቅት የመድረኩ አባል ለመሆን ወደኋላ የሚጎትት አንዳች ነገር የለም ሲሉ የነበሩ አባላቶች ስብሰባ ሲሆን አሁን ደግሞ ተጠና የተባለው ጥናት ግልባጩን ውጤት ነው በማለት ይዞ መጥቷል፡፡

መድረኩ ከተፈጠረ በኋላና ከመፈጠሩ በፊት የነበሩ በርካታ ሰነዶችን ለይተን አይተናል የሚለው ኮሚቴ የመድረኩ መተዳደሪያ ደንብ ሙሉ በሙሉ ዲሞክራሲያዊ ሆኖ አላገኘነውም ይላል፡፡ ይህ ደግሞ ከመድረክ ችግሮች መካከል መሰረታዊው እንደሆነ የጥናት ውጤቱ ያብራራል፡፡ በተለይም ሌሎች ፓርቲዎችን በማሳተፍ በእውነተኛ አካሄድ የሃገሪቱን የፖለቲካ ችግር በመፍታት በኩል ህገ ደንቡ ችግር እንዳለበት የኮሚቴው ጥናት አጽንኦት ሰጥቷል፡፡

ልብ በሉ ይህን የሚሉት የኮሚቴ አባላት በምርጫ 2002 ዋዜማ ላይ መድረኩን ሲያሞካሹና ከሰሞኑ ደግሞ የመድረኩን ማኒፌስቶ ሲያወለበልቡ የነበሩ ግለሰቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች እንደ አንድነት ኮሚቴ ቀደም ብለው ስላንቆለጳጰሱት የመድረኩ ፕሮግራም ሲናገሩ አሁን ባለው ሁኔታ የመድረኩ ፕሮግራም በአፋጣኝ ካልታረመ በስተቀር የአንድን ግንባር ፎርማሊቲ የሚያሟላ ሆኖ አላገኘነውም ይላሉ፡፡

ምክንያታችንም ሲሉ የጠቀሱት ደግሞ ቀደም ብሎም መድረኩ ሲቋቋም በርካቶቹ የፖለቲካ ምሁራን ያሉትንና አሁን ደግሞ ብለን ነበር የሚያስብላቸውን “በፖለቲካ መርህ ደረጃ ወሳኝ በሆኑ ሁኔታዎች ጫፍ የረገጡ ፖርቲዎች ናቸው ግንባር የፈጠሩት” የሚል ነው፡፡

ኢህአዴግ በምርጫ 2002 ዋዜማ ላይ ከመድረኩ ጋር ባደረጋቸው ክርክሮች መድረኩ ጥርት ያለ ፕሮግራም እንደሌለውና ቢኖረውም አንዱ ከአንዱ የተቀየጠና በፖለቲካ መርሆ በፍፁም ሊጣበቁ የማይችሉ ጉዳዮችን በማስትሽ በማጣበቅ ነው በምርጫው ገበታ ላይ ለመሳተፍ የሚታትረው፤ይህ ደግሞ የማያዛልቅና ማስትሹም የሚላቀቅ ነው ሲል እንዳልነበረና መድረኩም ለዚህ አስተያየት የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች እንጂ እኛ አይደለንም በማስትሽ ተያይዘን የመጣነው የሚል ምላሽ ሰጥቷል። የመድረኩ አንዳንድ ፕሮግራሞች የተድበሰበሱና ግልፅ ያልሆኑ ስለመሆናቸው በመመስከር በተለይ የመሬትና የፌዴራሊዝም ጉዳይ ወሳኝና አንገብጋቢ የፖለቲካ ጉዳዮች እንደሆኑም ይናገራል። እንዲሁም በቡድን እና በግለሰብ መብቶች ቅደም ተከተል ላይ ግልጽ የሆነ የፖለቲካ አስተሳሰብ ሳይያዝ ነው ግንባር ለመፍጠር የተሞከረው በማለት ማስትሹ በመላቀቅ ሂደት ላይ ነው ይላል የአንድነት ኮሚቴ ጥናት፡፡

መድረኩ ውስጥ የቡድን መብት ማስከበርን አስቀድመው የጋራ አላማ በማለት የሊብራሊዝም አስተሳሰብን ያስቀመጡ ፖርቲዎች መኖራቸው በጠላቴ ጠላት የተወዳጁ ስለመሆናቸው እንደሚያረጋግጥ በወቅቱ ኢህአዴግም ሆነ የፖለቲካው ዘርፍ ምሁራኖች ቢናገሩም አላየንም አልሰማንም ሲሉ የነበሩት የመድረኩ አባል ድርጅቶች ዛሬ "ጫፍ የረገጠ የርዕዮተ አለም ፍልስፍና እየተከተሉ ግንባር ማቋቋም ፈፅሞ አይቻልም" በማለት እየተናገሩ ነው፡፡

የአንድነት ፖርቲ ገምጋሚ ኮሚቴ ሲያሸረግድለት የነበረውን የመድረኩ ፕሮግራም በተፈረካከሰ ርዕዮተ አለም ግንባር ለመፍጠር የተሄደበት ርቀት የሁኔታውን አስገራሚነት ይበልጥ የሚያጎላ ነው በማለት በፕሮግራሙ ላይ ይሳለቃል፡፡ በአሁኑ ወቅት ስብሰቡ የግንባርነት ደረጃውን ሳይጨርስ ወደግንባር ማደጉ ትክክል አይደለም የሚለው ኮሚቴ መድረኩ ከግለሰቦችና ከቡድኖች በወጣ መንገድ ላይ እየተንቀሳቀሰ እንዳልሆነ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ የመድረኩ አባል ድርጅቶች ከግለሰቦች የንግድ ድርጅቶች ተለይተው አይታዩም ሲሉ የነበሩት የዘርፉ ምሁራን ይሄኔ ነው እንግዲህ "ብለን ነበር" ለማለት የሚገደዱት፡፡

አሁን መድረክ ስለሚባለው አንድ ስብስብ ከመጨነቅ በላይ ስለኢትዮጵያ ፓለቲካ እድገት መጨነቅ እንዳለብን የተረዳንበት አጋጣሚ ነው የሚለው ኮሚቴ በፕሮግራምና የደንብ ችግር ላይ የተመሰረተው መድረክ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ችግር የማይፈታ በመሆኑ ስብስቡ ይህንን የመተግበርና የማለፍ እምነት ካጣ መድረክ መፍረስ ነው ያለበት በማለት አንድነት ከመድረኩ ስብስበ የመጀመሪያው ወጪና የመድረኩን መፍረስ አርጂ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

መድረክ በመፍረስ ዋዜማ ላይ እንደሚገኝ ከሚያረጋግጡት ነጥቦች መካከል ዲሞክራሲያዊ ያልሆኑ ምልክቶች በስብሰቡ ውስጥ መታየታቸው ነው የሚለው ኮሚቴ በብሄር መደራጀት ዲሞክራሲያዊ መብታችን ነው ብለው የሚወስዱትና መብታቸውም እንደሆነ የተቀበልንላቸው ጉምቱ አመራሮች ህብረብሄራዊ ሆኖ መደራጀትን ዴሞክራሲያዊ ባለመሆን እየፈረጁት ስለመሆኑ አቶ ቡልቻ ደመቅሳና ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ በተለያየ ጊዜ አንድነት የአማራ ፓርቲ ነው - - - አንድነት ጠቅላይ ነው - - - አንድነት የከተማ ልሂቃን ፓርቲ ነው ወዘተ በማለት ለሚዲያ መናገራቸውን በማሳያነት አቅርበዋል፡፡

የመድረክ ፕሮግራም ውል የሌለውና በጨበጣ ስልጣን ላይ ለመውጣት በሚሹ ግለሰቦች የተፈበረከ እንደሆነ ሲነገራቸው አልሰማ ሲሉ የነበሩት የኮሚቴው አባላት መድረክ ከህዝብ ጋር ሳይሆን ከኢህአዴግ ጋር እየተወዳደረ በመሬትና በፌዴራሊዝም ጉዳይ ላይ ስልጣን ከያዝን በኋላ ህዝብ ይወስናል ፤በኋላ እንፈታዋለን ማለቱ መርህ የለሽ ፕሮግራም እንደሆነና በርግጥም በጨበጣ ስልጣን ላይ ለመውጣት ካለ ፍላጎት የመነጨ እንደሆነ በጥናት ውጤታችው ይፋ አድርገዋል፡፡ ይህንኑ የጨበጣ ስልጣን መሻት የበለጠ ግልጽ የሚያደርገው ደግሞ በመስኩ ረጅም ጊዜ በቆዩ ፖለቲከኞችና የዴሞክራሲ አርበኛ ማን እንደኛ በሚሉ ሃይሎች የተነደፈ ፕሮግራም መሆኑና በዚህም መድረኩ ባለፉት አራት አመታት አንድ ስንዝር መሄድ ያልቻለ ስብስብ መሆኑ ነው፡፡

የመድረክ አባል ድርጅት የሆኑት የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ(ኦህኮ) እና የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ(ኦፍዴን) ሊቀመንበር ዶ/ር መራራ መድረኩ በመፍረስ ዋዜማ ላይ ስለመሆኑና ማስቲሹም እየለቀቀ ስለመሆኑ ይፋ ያደረገውን ጥናት ፖለቲካ ባልገባቸውና በፖለቲካ መስክ ግራ በተጋቡ ግለሰቦች የተሰራ የመንገድ ላይ ስራ ነው በማለት አኮስሰውታል፡፡ ፕሮግራሙን በተመለከተም ደርዝ የለሽ ስለመሆኑ ያረጋገጠውን ጥናት በተመለከተ ዶ/ሩ እንደተለመደው “ኢህአዴግ ከሚቀልባቸው ሰዎች የሚነሳ ጥያቄ እንጂ የፖለቲካ ፕሮግራም ችግር የለብንም" በማለት ያለምንም ሃፍረት መናገራቸው በርግጥም በጨበጣ ስልጣን ስለመሻታቸው የሚያረጋግጥ ነው፡፡

የወቅቱ የመድረክ ሊቀመንበር አቶ ጥላሁን እንዳሻው ደግሞ ግምገማውን ህገወጥ በማለት የዘለፋ አስተያየት ይሰጡና እንዳውም ግምገማው የድርጅቱ(የአንድነት) የውስጥ ትግል ነፀብራቅ ነው በማለት ሊሸሹ ሞክረዋል። በእርግጥ ግምገማው የአንድነት የውስጥ ትግል ነፀብራቅ ሊሆን ቢችልም እንኳ መታየት ያለበት ስብስቡ በአጠቃላይ የጨበጣ ስልጣን ፈላጊ ህልመኛ ፖለቲከኞች የተሰገሰጉበትና በተፈረካከሰ ርዕዮተ አለም የሚነዱ ፓርቲዎች ያሉበት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ሲሆን አንድነትም ግምገማውን ሲያስቀምጥ ውጤቱ እንደአባል ፓርቲ እራሱንም እንደሚመለከት

ተቀብሎ መሆኑን ከግምት ከተን ስንመለከተው የዶ/ር መራራ ጉዲናና የአቶ ጥላሁን እንዳሻው አስተያየት ውሃ የማይቋጥር መሆኑን ያሳየናል፡፡

ይህ ደግሞ በአንድነት ፖርቲ በራሱ የውስጥ ችግርም ሆነ በማናቸውም መነሻ ምክንያቶች የተደረሰበት የግምገማ ውጤት ብቻ ሳይሆን አንድነቶች ምንም እንኳ ዛሬ አጠናነው ቢሉም ቀድሞም ቢሆን የሚያውቁትና ብዙዎቹ ብዙ ያሉለት ጉዳይ ነው፡፡ ምን ተብሎ ነበር? የሚለውን እንመልከት፡-

በህዳሴው ባቡር እንዳይሳፈር ሲታገሉት የነበሩት እና ከትግል መድረኩ የሸሹት ወገኖች በሂደቱ ተስበው የወጡት "የህዳሴ ልጆች" በህዳሴው ጎዳና በድል ተረማምደው፤ ምርጫ ዘጠና ሰባትን ተሻግረው፤ ከምርጫ 2002 ሲደርሱ፤ በህዳሴው መባቻ በአካል የታገላቸው ሃይል መልክ ቀይሮ እና ቅርፅ ሰብሮ በጣዕረ መንፈስ ሲታገላቸው ነበር በማለት አሜን የተባሉ ፀሐፊ "የሁለት ምርጫዎች ወግ" የተሰኘውን የአቶ በረከት ስምኦንን መጽሐፍ በዳሰሱበት ወጋቸው ላይ አስቀምጠዋል፡፡

ፀሐፊው ዳሰሳቸውን ሲቀጥሉ በ2002 ምርጫ ኢህአዴግ ስህተቶቹን አርሞ እንደወጣና የተቃዋሚው ጎራ ግን የአሰተሳሰብ ሳይሆን የመልክ ለውጥ ይዞ እንደመጣ የሚያጫውቱን አቶ በረከት "የጀብደኝነት ልጆች" እንዲህ ፈጥነው ከድርጅቱ ከወጡ በኋላ "መድረክ" በተሰኘው የፖርቲዎች ስብስብ ገብተውና እርሱን ወክለው በውድድር ቢቀርቡም በውድድሩ መሸነፋቸውን ያወጉናል በማለት መድረክን የተመለከተ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

በምርጫ 2002 ዋዜማ ላይ ከምርጫ 97 ቅንጅት የቀለም ለውጥ አድርጎ የመጣውን መድረክ ኢህአዴግ ሲገልጸው መድረክ የአገራችንን ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ፖሊሲ የሌለው፤ አለን የሚለውም ሃሳብ የአገራችንን ህዝቦች የፀረ ድህነት ትግል የሚቀለብስና ወደትርምስ የሚያስገባ ነው ይለዋል፡፡ በአለም አቀፍ የምርጫ ስነ ምግባር ራሱን ለማስገዛት ያልተዘጋጀው መድረክ በጨበጣ ስልጣን ለመያዝ የሚሻ ሃይልና አገር የመምራት ሃላፊነት ሊቀበል የማይችል እንደሆነም ኢህአዴግ በሚገባ ነግሮታል፡፡

በአገራችን የፖለቲካ ምህዳሩ እየሰፋ በመሆኑ በሃላፊነት መንፈስ ሊጠቀምበት ለሚፈልግ ሁሉ ምቹ እንደሆነ በጊዜው የገለፀው ኢህአዴግ ይሁን እንጂ እንደ መድረክ ያሉት ተቃዋሚዎች በዚህ እድል ከመጠቀም ይልቅ ያገኙትን እድል ሁሉ አገርን ለማተራመስ ሊጠቀሙበት ቆርጠው የተነሱ መሆናቸውን በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይህንኑ ሃሳብ "መድረክ የተሰኘውና በመድረኩ ጥላ ስር የተሰባሰቡ ፓርቲዎች የሃገራችንን ወቅታዊ ጉዳዮች በተለይም የዜጎችን መፈናቀል ለፖለቲካ ፍጆታና ጥቅም በማዋል ላይ ናቸው" ሲል ባለራዕይ የተሰኘ የወጣቶች ማህበር ገልፆ ፓርቲዎቹ

የሀገራችንን ፖለቲካ ወደፊት ሊያራምድ በሚችሉ አጀንዳዎች እንዲጠመዱና ይህንኑ በሚያሳኩ ፖሊሲና ፕሮግራሞች እንዲመሩ በማለት አጠናክሯል፡፡

አዲስ ታይምስ  የተሰኘ መጽሄትም መድረኩን እና የአመራር አባላቱን እንዲህ ሢል በአንድ ወቅት ገልጿቸዋል። መድረኩ ግራ በተጋቡ ፕሮግራሞችና ግራ በተጋቡ ግለሰቦች የተሞላ ሲሆን ይህንኑ ግራ የተጋባ መረጃ ለማግኘትም የሚቻልበት እድል እንደሌለና ድረ ገጽ እንኳ የሌለው በቀሽም አመራሮች የተሞላ ፓርቲ ነው በማለት ።በዚህም መክንያት የትም መድረስ እንደማይችልና አደጋ ውስጥ እንደሚገኝ የገለጸው መጽሄት ምናልባትም ብሎ ቀን ቆርጦ ሁሉ ነበር፣ ምናልባት ከ1ዓመት በኋላ ሊፈርስ እንደሚችል በመጠቆም። የመድረኩን የበላይ አመራሮች በተመለከተ ሎሚ መጽሄት ደግሞ እንዲህ ትለናለች"ተቃዋሚ መሪዎቻችን በረጅሙ የፖለቲካ ዘመናቸው ያመጡት ለውጥ የታለ?ብለን ለፍለጋ ብንነሳ የምናገኘው ውጤት ቢኖር ጠ/ር መለስ ዜናዊ "ሳስበው ሳስበው ደከመኝ "ብለው ለፓርላማቸው የጋበዙትን ቀልድ ነው።